# አያድርም ተኝቶ

ጠበቃ በቆመ ፤ ኢትዮጵያዬ ብሎ
ከሳሽ ከዳተኛ ፤ ንጹሀን ወንጅሎ
ፍርደ ገምድል ዳኛ ፤ ችሎቱን አስችሎ
በጨለማ እስር ቤት ፤ ከጉድጓድ አስጥሎ
በጨካኝ አለንጋ ፤ ገላው ተተልትሎ
ከሐገሩ ፍቅር ፤ የነፍስ ዋጋ ከፍሎ
ደም እየገበረ ፤ ፍትህ አገኝ ብሎ
ሰው እንዴት ይኖራል ፤ ችግር መከራ አዝሎ
ይለይለት እንጂ ፤ አንዴ ተቀጣጥሎ ።

አገሬ ኢትዮጵያ ፤ ጸናብሽ ሀዘኑ
ከትውልድ ትውልድ ፤ በማያልቅ ዘመኑ
የእንግዴ ልጅ ወልደሽ ፤ ዘምቶ በወገኑ
ልጆችሽ ሲቆሉ ፤ በሳት ሲፈተኑ
እንኳን ወታደሩ ፤ ጨክኖ ካህኑ
የንኩሮ መጋፊያ ፤ ከሆነ ሚዛኑ
ጨለማው ሲረዝም ፤ አልነጋ ሲል ቀኑ
ካጽናፍ ፤ እስከ አጽናፍ ፤ በየማዕዘኑ
አቀጣጥሉ እሳቱን ፤ ይታይ ውጋጋኑ
ነገማ ይረፍዳል ፤ ይጀመር ካሁኑ ።

ቀድሞ የማናውቀው ፤ አዲስ ባህል መጥቶ
አገሩን ሸንሽኖ ፤ ቆራርጥ በልቶ
ከባዕድ ሲሸጠው ፤ ወንድሙን ቀምቶ
ይህን ሁሉ እያየ ፤ ይህን ሁሉ ሰምቶ
አገርማ አልተኛም ፤ አለ እንጂ አድብቶ
ይመከራል ይዘከራል ፤ ዝናሩን አንግቶ
ቀን እየጠበቀ ፤ ይሆናል ዘግይቶ
አገር እንደዋዛ ፤ አይቀርም ተረስቶ
ያራት ኪሎው ጅኒ ፤ ባፍ ጢሙ ተደፍቶ
አጫፋሪው ሁሉ ፤ ታስሮ ተጎትቶ
ያቺ ቀን ሳትመጣ ፤ አያድርም ተኝቶ ።

አራት ኪሎን ይዞ ፤ ዝንባም ባለ ቁምጣ
የገዛ ወገኑን ፤ አድርጎ ባላንጣ
በትዕቢት አበጠ ፤ ዘለለ እንደ ፌንጣ
ድንበሩን ሸንሽኖ ፤ ሸጠው እንዳወጣ
ሕዝቡን እያስራበ ፤ በጠኔ እየቀጣ
ማን አለብኝ ብሎ ፤ ድፍረቱ ቅጥ አጣ

EthioLion.Com

ሰው ሁለቴ አይሞትም ፤ የመጣው ቢመጣ
በደሉ ይሰማህ ፤ እንቢ በል ተቆጣ
በክርንህ ደቁሰው ፤ ይሄንን ማጋጣ
ከነ ቅራቅንቦው ፤ ጠራርገ እስኪወጣ
በሰፈረው ቁና ፤ ተሰፍሮ እስኪቀጣ ።

ደደቢት አይደለ ፤ ያለው አዲሳባ
ገርበብ ብሏል በሩ ፤ በርግድና ግባ
ካቴ የከበደው ፤ የወያኔ ቱባ
ሰው መስሎ የሚታየው ፤ በምጽዋት ካባ
ቢከፍቱት ቀፎ ነው ፤ ባዶ ነው ገለባ
ሲርድ ታየዋለህ ፤ እንደያዘው ወባ
እናቴ ማህጸን ፤ ተመልሶ አይገባ
ያፈሰሷትን ደም ፤ ያፈሰሷት እንባ
ሳይከፈል አይቀር ፤ ሆና በጥፍ አርባ ።

የደደቢት ቂጥኝ ፤ ሽብቦ የያዛችሁ
ይሻላል ብትኖሩ ፤ ውርደ ተብላችሁ
መቃብር ከመውረድ ፤ ከሙት ወግናችሁ
ከሕዝብ መታረቅ ፤ ፍላጎት ካላችሁ
የጎሳ የመንደር ፤ ተረት አቁማችሁ
ከሕዝባችን ጥሪ ፤ አጽንዖት ሰጥታችሁ
እራስን ለማዳን ፤ ስሙት ሲጠራችሁ
በናቴ መቀነት ፤ እንዳይመሽባችሁ
በሆድ ማሰብ ቀርቶ ፤ ያስብ አይምሯችሁ
ማዕበል ተነስቶ ፤ ሳይጠራርጋችሁ
ታሪክም በናንተ ፤ እንዳይፈርድባችሁ
አመዛዝኖ ፈራጅ ፤ ህሊና ይስጣችሁ ።

ታዛቢው

EthioLion.Com